## <u>ፓኖራማ ቁጥር 81</u>

የትዝብት አድማስ

ኅዳር ቀን 6 2002 ዓም

## <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመርጠው ምርጫ</u>

በየትኛው ሀገር የሚኖሩ የህገ-መንግሥት ጉዳዮች ምሁራን፥ የፖለቲካ ሳይንስ ጠቢባን፥ የህግ ባለሙያዎችና ጠበቆች ሁሉ የሚስማሙበት አንድ መሠረታዊ ሀቅ ቢኖር፥ የማንኛው ሀገር የበላይ ህግ ተብሎ የሚጠራው፥ የዚያው ሀገር ህገ መንግሥት መሆኑን ነው ። በዚህ ህገ መንግሥት ላይ በመመስረት ልዩ ልዩ ህግጋት ፥ ደንቦችና ሥነሥርዓቶች ይወጣሉ ። እነርሱም የህገ-መንግሥቱ ግልገሎች ተብለው ይጠራሉ ። ግን ዞሮ ዞሮ ደግሞ የሀገሪቱ ህገ መንግሥት ፥ የዜጎቹን የማፅደቅ ድምፅና ተቀባይነት ለማግኘት የሚችለው ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኖ የሕዝቡን ተሳትፎንና ውሳኔን ሲያገኝ ብቻ ይሆናል ። ይህ ማለት ደግሞ የምርጫ ህጎች ፥ ደንቦች ሥነ ሥርዓቶችና ስምምነቶች የህገ-መንግሥቱ ተገዥዎችና አክባሪዎች መሆናቸው ሲረጋገጥ ነው። ወጣም ወረደ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈንና መረጋገጥ ዋስትና መኖሩን ዜጎች አምነው ሲቀበሉ ይሆናል ። እንግዲህ ፥ በየትኛውም ሀገር፥ስለ ምርጫና ከርሱም ጋር ተያይዘውና ተከትለው ስለሚመጡ ጉዳዮች ከመነገሩ አስቀድሞ፥ከላይ ባጭሩ የተጠቀሙት መሠረታዊ ጎዳዮች ተሟልተው እንዲገኙ ግድ ይላል ። የእነርሱ ሁሉ መሠረት ፥ ግድግዳና ጣሪያ፥ የሀገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ለመሆኑ ማንም ዜጋ ሊከራከር አይችልም ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነት፥ ዛሬ እነኝህ መሠረታዊና ዐበይት ጉዳዮች በሀገራችን ውስጥ በጭራሽ የሉም ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ፥ ከወያኔና ከአንዳንድ የፖለቲካ ተዋንያን ጋር የሚለየው ይህ መሠረታዊ የዕምነት ቅራኔ ነው ። ይህ መሠረታዊ ልዩነት እስካልተፈታ ድረስ ደግሞ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመርጠው ምርጫ ሊኖር አይችልም ። ጨርሶ!

በኢትዮጵያ ተፈራራቂ የፖለቲካ ተዋናይን ስለ ምርጫ የነበራቸውና አሁንም ያላቸው ዕምነትና ገቢር፥ በመሠረታዊ መልኩ ልዩነት የለውም። የነኝህ ሥርዓት አራማጆች መነሻና መድረሻ፥ ማጠየቂና ማጣቀሻ፥ ምንጊዜ ቢሆን የዜጎች መብትና ነፃነት ፥ ፍላጎትና ምኞት ሳይሆን የራሳቸውን ሥርዓትና አገዛዝ ፍላጎትና ተልዕኮ ማሳካት ነው ።ህገ መንግሥት ብለው ለሚጽፉት ሰነድ መሠረት የሚያደረጉት፥የዐዔው ሥርዓት ፈጣሪን፥ ( ስዩመ-እግዚአብሔር)

ሲሆን፥ ህግ መንግሥት የሚሰጠው ከነገሥታት በመነጨ በጎ ፈቃድ እንጅ ፥ ከሕዝብ ተሳትፎና ውሳኔ መሆኑን የሚክድ አስተሳሰብ ነው ። ደርግ በበኩሉ ፥ ከዐብዮት ያገኘነው የታሪክ ኃለፊነት አለብን በሚል ማጠየቂያ የአባገነን ማጠናከሪያ ሰነድ አጽፎ ህገ መንግሥት ብሎ አመጣ። ወያኔ ደግሞ ብሄርንና ዘርን ተመርኩዞ ዘረኝነትን ህጋዊ የሚያደርግ ሰነድ አጽፎ መጣ ። ሁሉም ሥርዓቶች፥ ሕገ መንግሥት ብለው ለሚጽፏቸው ሰነዶች ምክንያት የሚያደርጓቸው የተለያዩ መመርኮዣዎች ቢኖሯቸውም ፥ ሥርዓታቸው ግን ያው ከአምባገነንነት አያልፉም ። በተለያዩ አመጣጦችና ምክንያቶች ላይ ተመርኩዘው የሚጻፉ ሰነዶች ደግሞ፥ በምንም መስፈርት ቢመዘኑ፥ ህገመንግሥት ናቸው ሊባሉ አይችሉም ። እስከዛሬ እነኝህ የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች ህገመንግሥት እያሉ የሚጽፏቸው ሰንዶች ሁሉ የየሥርዓቶቻቸው ማራመጃና ማስፈጸሚያ ቀላጤዎች እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቃቸው፥ የሚያከብራቸውና የሚገለግልባቸው አይደሉም ። ምንም እንኳ በዓለም የታሪክ ሂደት ፥ በስመ ሥልጣኔ ፥ ሃይማኖት፥ ዐብዮት፥ ዴሞክራሲ፥ ነፃነት፥ ርመጃ ወዘተ በርካታ ግፍና በደል የተፈፀሙ መሆናቸው ባይካድም፥ በዛሬይቱ ዓለማችን አያሌ ዜጎች ከእነኝህ በደሎችና ግፎች የተላቀቁ ለመሆናቸው አሌ የሚባል አይደለም ። በኢትዮጵያ ሀገራችን ግን መልካቸውንና ቅርፃቸውን ለየወቅቱ መለዋወጥ እንዲያመቹ ተደርገው በሚቀርቡ ምክንያቶች፥ተዘርዝረው የማያልቁ በደሎችና ግፎች መፈፀማቸውን ቀጥለዋል ። በህገ መንግሥት አስመሳይ ሰነድ፥ የህግ ሽፋን እያገኙ እልቂትና ጥፋት፥በደልና ጭቆና መፈፀም በሀገራችን ኢትዮጵያ ያልተለመደ ነው ባይባልም ፥ በዛሪይቱ ኢትዮጵያ ያሉት የዘረኝነት ሥርዓት አራማጆች ግን፥ ሕዝብና ሀገርን የሚጎዳ ዐይን ያወጣ ወንጀል እየፈፀሙ ይገኛሉ ። ታሪክና ትውልድ የማይረሳው የሀገር ጥፋት መፈፀማቸው ብቻ ሳይሆን ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያላቸው ንቀት ፍራቻና ጥላቻ፥ባዕዳን ቅኝ ገዥዎች ጭምር እንጅ የሀገር ውስጥ አምባገነኖች ብቻ እንደሆኑ አያስቆጥራቸውም ። ታዲያ በየጊዜው የምርጫ ድግሳቸውን የሚያሰናዱት የምዕራብ አለቆቻቸውን መመሪያና ትዕዛዝ ለመፈጸምና ይህንንም በማድረጋቸው ለሚሰጣቸው ጉርሻ ሲሉ የሚጎናበሱት ሽርጉድ እንጅ፥የኢትዮጵያን ሕዝብ የዴሞክራሲ ሥርዓት ጥም ለማርካት አይደለም ። በመሆኑም ፥ በራሳቸው ድግስ ጭፈራ የሚያደምቁላቸውን ጋሻ ጃግሬዎችና የድግሳቸው ወጥ ቀማሾችን ቢያሰልፉ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቶ አይደንቀውም ። ወያኔዎቹ ምርጫ ሲሉና የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ሲል መሠረታዊና የማይታረቁ ልዩነቶች አሉ ። ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- በዴሞክራሲ ሕገ መንግሥት ላይ የተመሠረተና መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የወከለ ሕዝባዊ መንግሥት እስከሌለ ድረስ ትክክለኛ ምርጫ የሚባል ነገር ቀልድ ነው። ወያኔ ደግሞ እንኳንስ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ታግየለታለሁ የሚለውን የትግራይንም ሕዝብ ቢሆን

የሚወክልበት ህጋዊ ምርኩዝ የለውም፡፡ዴሞክራሲያዊ ህገመንግሥትና ሕዝብን የሚወክል መንግሥት በሌለበት ሁኔታ ምርጫ ብሎ ነገር የለም፡፡

- ዴሞክረሲያዊ ሥርዓት ተረጋግጦ ሕዝብ ያለስጋት የሚሳተፍበት ምርጫ እስካልተመቻቸ ድረስ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውነተኛ ወኪሉን ይመርጣል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም ፡፡ በጎሳ ክልል እንዲሸበበ የተደረገ ዜጋ ሌላውን ኢትዮጵያዊ ዜጋውን የሚመርጥበት ዕድሉ ስለ ተዘጋበት ብሔራዊ ምርጫ ሊያካሂድ አይችልም ፡፡ በዘር ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ ምርጫ ለማከናወን አይሆንለትም፡፡ማነኛውም ኢትዮጵያዊ፥ በሰብዓዊነቱ ብቻ ሳይሆን፥ በኢትዮጵያዊ ዜግነቱ እርሱ በመረጠው ቦታ ለመኖር የተከለከለ መሆኑን እያወቀ፥ ብሔራዊ፥ ነፃና ርቱዕ ምርጫ አካሄዳለሁ ብሎ ራሱን አያታልልም፡፡

- መሠረታዊ የሆኑ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ የአንድ ዜጋ የህግ ብቻ ሳይሆኑ የተፈጥሮ መብቶቹም ጭምር በመሆናቸው፥ እነርሱን የሚያስከብሩ የህግ የበላይነትም ሆነ የሰው ልጅ ልዕልናን አስከብረው የሚከበሩ የነፃነት ፋናዎች በሀገራችን ውስጥ ዛሬ የሉም፡፡ ታዲያ በቅድሚያ የነርሱን መኖር ሳያረጋግጡ ፥ ብሔራዊ ምርጫ ቀርቶ ፥ የአንድ ዜጋ በህይወት የመኖር/ያለመኖር ምርጫ መውሰድ እንኳን አይኖርም፡፡

- የኢትዮጵያ ብሔራዊና ፖለቲካዊ ነጻነት በባዕዳን የጅአዙር ቅኝ ግዛት መውደቁ ብቻ ሳይሆን፥የግዛት አንድነት፤የዜጎቿ አንድነትና እኩልነት ሀገራዊ ልዋላዊነት ፤መናጋቱ የሀገሪቱን ኀልውና በአስጊ ደረጃ ላይ ጥሎታል፡፡ይህም በመሆኑ፥ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቅድሚያ ብሔራዊ አጀንዳው ፥ ሀገሩን ከጥፋት ማዳን መሆኑን አጥብቆ ያምናል ፡፡ ሁኔታውንም ለመለወጥ የሞት-ሽረት ትግል እያካሄደ እያለ ፥ በወያኔ የቀልድ ምርጫ ለመሳተፍ የቅድሚያ አጀንዳውና ዓላማው ሊሆን ከቶ አይችልም፡፡

በመሆኑም የወያኔን ምርጫ እንደ ጨረባ ተስካር ከመቁጥር በቀር ቁም-ነገር አይሰጠውም።

በነኝህ ዐበይትና መሠረተዊ ምክንያቶች፥ የወያኔ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ሊሆን አይችልም። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፎ ወያኔን የሚታገለውም ኢትዮጵያዊ ኃይል፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በምርጫው ያለመሳተፍን ውሳኔ ያከብራል ። ይደግፋል ። በወያኔ ምርጫ ለመሳተፍ የማይፈልጉት ክፍሎች መኖራቸውና የሕዝብን ተቃውሞ መደገፋቸው መብታቸው ነው ። በአንፃሩ ደግሞ፥ በወያኔን ምርጫ ለመሳተፍ የተሰለፉና የእነርሱንም ፈለግ ለመከተል ያቆበቆቡ ቡድኖች እንደሚኖሩ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ አይደለም።

“ በሉ አናንተም ሂዱ እኛም ወደዚያው ነው፥
ወትሮም መንገደኛ ፊትና ኋላ ነው። ”

እየተባለ የሚዘመረው የሰሞኑ ዜማ ያለምክንያት እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትዝብት ይገነዘብላቸዋል። የወያኔ ምርጫ ግን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመርጠው ምርጫ አይደለም። በመጪው የወያኔ ምርጫ ተብዬ ሂደት አለመሳተፍ ብቻ ሳይሆን፥ መርጫውንም መቃወም፥ የዜግነት መብታቸውና ግዴታቸው መሆኑን ፥ ወያኔን የሚታገሉ ኃይሎች አጥብቀው ያምኑበታል።